Asylum Support Partnership
help and advice

refugee action | North of England Refugee Service | Refugee Council | scottish refugee council | Welsh Refugee Council Cyngor Ffoaduriaid Cymru

March 2012 Amharic

# ለጥገኝነት ማመልከት

እንግሊዝ አገር ውስጥ ጥገኝነት ለማግኘት ጥያቄ ሲያቀርቡ፡ ለባለሥልጣኖቹ (የአገር ውስጥ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት) እንደ ስደተኛ ታዋቂነት እንዲሰጥዎት ጠይቀዋል ማለት ነው። ስደተኛ የሚለው ቃል ትርጉሙ የተወሰደው፡ የስደተኞች የመኖርያ ሁኔታ በተመለከተ የ1951 የተባበሩት መንግስታት ስምምነት ተብሎ ከሚጠራው አለም አቀፋዊ የሆነ ሕግ አንድ ክፍል ነው። የእንግሊዝ አገር መንግስት እርስዎ እንደስደተኛ ከለላ ለማግኘት ብቁ መሆንዎንና አለመሆንዎን ይወስናል። የእንግሊዝ ምንግስትየስደተኛነት ፍቃድ እንዲያገኙ ለመወሰን ግን እርስዎ ወደ አገርዎ ከተመለሱ በዘርዎ፡ በሃይማነትዎ፡ በብሄርዎ፡ የአንድ ማህበር አባል በመሆንዎ ወይም የተለየ የፖለቲካ አስተያየት ስላልዎት በደል ወይም ስቃይ ሊደርስብዎት ይችላል ብሎ ካመነ በኋላ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፡ በእንግሊዝ አገር እንዲኖሩ የሚያደርግዎት ሌላ የሰብአዊ ጉዳይ ወይም የሚያስገድድዎት ምክንያት ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ተቀባይነት ካጣ፡ የአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት (European Convention on Human Rights) መሰረት ሰብአዊ መብትዎ አልተከበረም ማለት ነው። የህግ አማካሪዎ ይህ ጉዳይ እርሶን ሊመለከት እንደሚችል ወይም እንደማይችል ማሳወቅ መቻል አለበት፡፡ እነዚህ የጥገኝነትና የሰብአዊ መብቶች ህጎች የተወሳሰቡ ነገሮች ስለሆኑ ጥሩ የህግ ምክር የሚሰጥና ወኪል የሚሆንዎት አማካሪ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የህግ ምክርና ውክልናን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ፡ እባክዎን በዚህ ጽሑፍ ገጽ 5 ላይ ይመለከቱ። ለጥገኝነት በሚያመለክቱ ጊዜ፡ በባለሥልጣናቱ "ጥገኝነት ጠያቂ" ብለው ይጠራዎታል። ከ 18 ዓመት በታች እድሜ ከሆኑና ለጥገንነት በግልዎ ካመለከቱ ጉዳይዎ ወደ የማህበራዊ ጉዳይ አገልግሎት (social services) ወይም ወደ ስደተኛ ማእከል ይላካል።

## የጥገኝነት ጥያቄ የሚመለከተው አካል ማን ነው?

በእንግሊዝ አገር፡ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስተር (Home Office) አካል የሆነ የእንግሊዝ አገር ድንበር ወኪል (UK Border Agency - UKBA) ለጥገኝነት የሚያመለክቱ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ የማድረግና ማመልከቻቸውን የመመርመር ሃላፊነት አለው።

## ለጥገኝነት እንዴት ነው የማመለከተው?

**ወደ እንግሊዝ አገር በገቡበት ጊዜ ተሎ ብለው ለጥገኝነት ማመልከትና የህግ አማካሪ መፈለግ በጣም አስፈላጊ ተግባሮች ናቸው።**

ለጥገኝነት ለማመልከት የሚችሉባቸው መንገዶች:

- ወደ አገሩ በሚገቡትበት ጊዜ፡ አውሮፐላን ማረፍያው ወይም በባህር ወደብ ላይ የሚገኘው የኢምግሬሽን ባለሥልጣን በማሳወቅ ለማመልከት ይችላሉ፡ ወይም
- ወደ እንግሊዝ አገር ከገቡ በኋላ፡ በ Croydon በሚገኙት የድንበር ወኪል ጽሕፈት ቤቶች በአካል ሄደው ለማማልከት ይችላሉ። ይህም ወደ አገሪቱ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወይም ደግሞ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለምሳሌ፡ የተማሪ፣ የጉብኝት፣ወይም የንግድ ቪዛ አግኝተው የገቡ ሊሆኑ ይችላሉ። የክረይደን የጥገኝነት ማጣርያ ክፍል (The Croydon Asylum Screening Unit) አድራሻው፡ **Lunar House, 40 Wellesley Road, Croydon CR9 2BY** ነው።
- በጣምለ ለየት ባሉ አጋጣሚዎች የጥገኝነት ማመልከቻዎ በአካባቢያዊ ህግ አስፈጻሚ ቢሮ (Local Enforcement Office) ሊቀዳ ወይም በስክሪን የሚታይ የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ ተንከባካቢ የሌላቸው ህጻናት እና አሳማኝ በሆነ ምክንያት ወደ ክራይዶን (Croydon )እንዲቀሳቀሱ የማይጠበቅባቸው ላይ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በእርሶ ላይ ሊሰራ እንደሚችል ለማወቅ በአካባቢዎ የሚገኘውን የስደተኞች ወኪል ያነጋግሩ፡፡

በጥገኝነት ማጣሪያ ክፍል የጥገኝነት ማመልከቻ ለማቅረብ ከፈለጉ ቀጠሮ ለመያዝ በስልክ ቁጥር **020 8196 4524** መደወል አለብዎ፡፡ ያለ ቀጠሮ በመጡበት ቀን UKBA ሊያነጋግርዎ እንደሚችል ምንም አይነት ማረጋገጫ የለም፡፡

ቀጥሎ ባለው ድርጣቢያ ላይ ሌሎች የመረጃ ጽሑፎች ሊያገኙ ይችላሉ፡ http://languages.refugeecouncil.org.uk
Asylum Support Partnership is a partnership project hosted by the British Refugee Council
British Refugee Council, (commonly called the Refugee Council) is a company limited by guarantee registered in England and Wales, [No 2727514] and a registered charity, [No 1014576].
OISC No: N200100132 Community Legal Service

## ለጥገኝነት ሳመለከት  ምን ይከተላል?

የ UKBA  ጽህፈት ቤት የጥገኝነት ማመልከቻዎችን በተለያየ መንገድ ያዩታል። አንዳንድ ማመልከቻዎች ወዲያውኑ ሊታዩ ይችላሉ። ስለሆነ የሚያቀርቡትን ማመልከቻ እንዴት እንደሚታዩት የUKBA  ጽህፈት ቤት የማጣራት ቃለመጠይቅ ተብሎ የሚታወቀውን የመጀመርያው ቃለ መጠይቅ ካደረገሎት በኋላ ይወስናል። አስተርጓሚ የሚስፈልግዎት ከሆነ ሊቀርብሎት ይችላል። በተጨማሪም የሴት ወይም የወንድ አስተርጓሚ ለመምረጥ ይችላሉ።

## የማጣራት ቃለ መጠይቅ በሚካሄድበት ጊዜ ምን ይከሰታል?

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአገር ውስጥ ጽህፈት ቤት UKBA ስለእርስዎ መደበኛ ግላዊ መረጃ ጤንነትዎ እና ወደ እንግሊዝ አገር እንዴት እንደገቡ እና የተሳተፉባቸውን ህገወጥ ድርጊቶችለመጠየቅ ነው። ለምን ወደ እንግሊዝ እንደመጡ እና ወደአገርዎ ለምን መመለስ እንደማይችሉ ይጠየቆታል ነገርግን ለምን ለጥገኝነት እንዳመለከቱ የሚያሳዩ ዝርዝር የሆኑ ጥያቄዎች ሊጠይቁ አይገባም። አብዛኛዎቹ በምርመራ ቃለመጠይቅ ላይ ያስገቧቸው መረጃዎች በድጋሚ የጥገኝነት ቃለመጥይቅዎ ላይ ይጠየቃሉ ሁለቱ መረጃዎች የሚለያዩ ከሆነ ይህንን እንዲያስረዱ ይጠየቃሉ፡፡

### የግል ዝርዝር መረጃዎችና ስነዶች

ማንኛውም ከእርሶ ጋር ጥገኛ የሆኑ ሰዎች ካሉ፡ ለምሳሌ፡ ሚስትና ልጆች ካልዎት ደግሞ፡ በማመልከቻዎ ውስጥ  እንዲመዘገቡ ወደ ማጣራት ቃለመጠይቅ በሚመጡበት ጊዜ አብረዎት መምጣት አለባቸው። ቃለመጠይቁ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል ከቻሉ ምግብ እና መጠጥ ይዘው ይምጡ፡፡

እርስዎ እንግሊዝ ለመግባት የተጠቀሙበት ስምዎ እና ዜግነትዎ የተፃፈበት ትክክለኛ ሰነድ እንዳለዎ UKBA ስምዎ ያረጋግጣል፡፡ ይህ ፓስፖርት ወይም ሌላ የመታወቂያ ሰነድ ሊሆን ይችላል፡፡ ትክክለኛ የሆነ የመታወቂያ ሰነድ ከሌልዎ ለምን እንደሌልዎ በተቻለ መጠን በአግባቡ በተብራራ ዝርዝር መግለጽ አለብዎ፡፡

በዚህ የማጣራት ቃለመጠይቅ ጊዜ የUKBA  ጽህፈት ቤት፡ የጣት አሸራዎንና ፎቶግራፍዎን በመውሰድ የማመልከቻ መመዝገብያ ካርድ (Application Registration Card - ARC) የሚባለው ካርድዎ ላይ ይለጥፉታል። አብዛኛውን ጊዜ ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት ይህ ARC ካርድ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ካርድ ደግሞ እርስዎ የጥገኝነት አመልካች መሆንዎን ያመለክታል፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ከጠየቁ በየሳምንቱ ገንዘብ ለመውሰድ ይጠቀሙበታል፡፡ ይችላል። አንዳንድ ጉዳይዎች ላይ የUKBA  ጽህፈት ቤት ይህን ARC  የሚባለውን ካርድ ላይሰጥዎት ይችላል። መንትኩ ግን የጥገኝነት ጠያቂ መሆንዎን የሚገልጽ ህጋዊ የእውቅና ደብዳቤ (Standard Acknowledgment Letter - SAL) ሊሰጥዎት ይችላል።

አብዛኞቹ የጥገኝነት ጠያቂዎች IS96 የሚባለው ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። ይህ ደብዳቤ የሚገልጸው ደግሞ፡ እርስዎ ጉዳይዎ/ማመልከቻዎን ባለሥልጣኖቹ እስኪያጣሩት ድረስ በጊዚያዊነት እንግሊዝ አገር ለመኖር እንደተፈቀደሎት የሚያሳይ ነው። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ላይ ሁልጊዜ ሪፖርት ወደማድረጊያው ማእከል እየሄዱ ሪፖርት ማድረግ ይገባል። ባለሥልጣኖቹ እንግሊዝ አገር በገቡበት ጊዜ ስምዎንና ዜግነትዎን የሚገልጽ ህጋዊ የሆነ ወረቀት እንዳልዎት ያጣራሉ። ይህ ወረቀት ደግሞ ፓስፖርት ወይም ሌላ የመታወቂያ ወረቀት ሊሆን ይችላል። ህጋዊ የሆነ ወረቀት ከሌልዎት፡ ለምን እንደሌልዎት በተቻለ መጠን በዝርዝር ማስረዳት አለብዎት።

### የመጡብት ቦታ

የማጣራት ቃለመጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ፡ ባለሥልጣናቱ ከእንግሊዝ አገር ሌላ የእርስዎን የጥገኝነት ጥያቄ ሃላፊነት የሚወስድ ሌላ አገር ካለ ይወስናሉ። ለምሳሌ፡ የUKBA  ጽህፈት ቤት እርስዎ ወደ እንግሊዝ አገር በሚመጡበት ጊዜ በሌላ አገር በኩል የመጡ ከሆነ እዛ አገር ውስጥ ለጥገኝነት ማመልከት ይችሉ ነበር ብሎ ካመነ ነው።

### የሚያቀርቡትን ማመልከቻ በፍጥነት ሊታይ ይችላልን?

ባለሥልጣናቱ ያቀረቡት ማመልከቻ በፍጥነት መታየት አለበት ብለው ካሰቡ፤ ማመልከቻዎን በአስቸኳይ የውሳኔ አሰራር ይታያል። ሁኔታው ይህ ከሆነ፡ ባለሥልጣናቱ ውሳኔያቸውን ሙሉ በሙሉ እስኪሰጡ ድረስ ወደ ሃርሞንድስዎርዝ የመጠለያ ማእከል (Harmondsworth Removal Centre) (ለወንዶች) ወይም ያርልስ የመጠለያ ማእከል (Yarl's Wood Removal Centre) (ለሴቶች) ሊያሸጋግርዎት ይችላሉ። በእነዚህ መጠለያ ውስጥ ካሉ፡የህግ አማካሪ ይዘጋጅሎታል፡ እንዲሁም የጥገኝነት ጥያቄዎ በፍጥነት መልስ ይሰጠዋል። ሆኖም ግን በፍጥነት የሚወሰኑ ማመልከቻዎች ያሏቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች በሙሉ በመጠልያ ውስጥ ይቆያሉ ማለት አይደለም።

## የጥገኘኘት ማመልከቻዎ በተቻለ መጠን በጊዜው አስገብተዋልን?

የUKBA  ጽህፈት ቤት እንግሊዝ አገር ውስጥ ከገቡ በኃላ የጥገኝነት ማመልከቻዎ በተቻለ መጠን ቶሎ ብለው ያስገቡ እንደሆነ ያጣራሉ። የዚህ መልስ 'አይደለም' ከሆነ፡ ከመንግስት የሚሰጦት የመኖርያ ቤት እና/ወይም የመኖርያ ድጎማዎችን ላያገኙ ይችላሉ። ስለ ጥገኝነት እርዳታ ተጨማሪ መረጃ ከፈልጉ፡ 'ለጥገኝነት ድጋፍ ማመልከት' የሚለውን ጽሁፍ ቀጥሎ ባለው ድረገጽ ማንበብ ይችላሉ። http://languages.refugeecouncil.org.uk

**በተጨማሪም፡ የማጣራት ቃለመጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ፡ አብዛኛው ጊዜ ቀጥሎ ያሉት ነገሮች ይከናወናሉ፡**

- የUKBA ጽህፈት ቤት ባልሥልጣን የጉዳዩ ባለቤት ('case owner') በመባል የሚታወቀው ስምና ስልክ ቁጥር ሊስጥዎ ይገባል። ይህ ባለሥልጣን ደግሞ ጉዳይዎን ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ይከታተላል። የጉዳይ ሰራተኛው ከእርስዎ ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግና ለማመከቻዎ ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለው። በተጨማሪም ይህ የጉዳይ ባለሥልጣን የሚባለው ሰው የሚያስፈልግዎትን የማህበራዊ ዋስትና ፍላጎቶች እንዲያገኙ፡ አወንታዊ የሆነ ውሳኔ ከተሰጥዎት ደግሞ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲቀላቀሉ ወይም ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካጣ ደግሞ ለቀው ለመውጣት ይተባበርዎታል። ይህ የጉዳይ ባለሥልጣን ለእርስዎ ወይም ወኪልዎ ዋና የመረጃ ምንጭ ነው።
- የህግ አማካሪ የማግኚያ መንገድ ሊለያይ ይችላል። የሕግ አማካሪ ለማግኘት አድራሻና የቀጠሮ ቀን ወይም የህግ አማካሪዎች ዝርዝር ስም ሊሰጥዎት ይችላል።
- በማጣራት ቃለመጠይቅ ላይ የተወሰዱ የማስታወሻዎች ቅጂ ሊሰጥዎት ይገባል።
- ባለሥልጣኖች ስለ ጥገኝነትና እንግሊዝ አገር ውስጥ ኑሮ የበለጠ መረጃ የሚሰጠውን 'ማስተዋወቂያ' ('induction') ወደሚባለው ፕሮግራም ሪፖርት እንዲያደርጉ ሊያሳውቅዎት ይገባል።

UKBA ስላሉት አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡ የገንዘብ ድጋፍና የመኖርያ ቤት) ወይም ሊያገኟቸው የሚገባ አገልግሎቶችን በተመለከተ በ 15 ቀኖች ውስጥ ሊያሳውቅዎት ይገባል። በተጨማሪም ምክር ሊሰጥዎት ስለሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበሮች እና ሌሎች ህጋዊ ድጋፍ የሚሰጡ ማህበሮች መረጃ ሊያቀርብሎት ይገባል።

## በጥገኝነት ቃለመጠይቅ ላይ ምን እርምጃ ይወሰዳል?

ከማጣራቱ ቃለ መጠይቅ ቀጥሎ፡ UKBA ለጥገኝነት ያስገቡት ማመልከቻ በተመለከተ ሊጠይቅዎት ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ እንዲመጡ ይጠይቆታል። ከቃለ መጠይቁ በፊት ከህግ አማካሪ ጋር መመካከር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ ጊዜ ላይ አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እንዲገኝ መጠየቅ ይገባል። እንደየፍላጎትዎ ደግሞ ወንድ ወይም ሴት አስተርጓሚ እንዲዘጋጅሎት ለመጠየቅ ይችላሉ።

ይህ ቃለ መጠይቅ እርስዎ ለምን ወደ እንግሊዝ መምጣት እንደፈለጉ እና ወደ ትውልድ ሃገርዎ ለምን መመስ እንደማይፈልጉ ለማብራራት በጣም አስፈላጊ እድል የሚሰጥዎ ነው፡፡ ስለ ጥገኝነት ማመልከቻዎ በተቻለ መጠን በርካታ ዝርዝር ነገሮችን መስጠት አለብዎ ፡፡ ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ማስገባት አለብዎ፣ ለምሳሌ፡ የህክምና መዝገብ ወይም የአገርዎ ሁኔታን የሚያሳይ ጋዜጣ ላይ የወጡ ጽሁፎች ካሉ ደግሞ ማቅረብ ይገባል። ነገርግን ያቀረቡትን መረጃ በሙሉ ማመልከቻውን የሚደግፍ እንጂ ተቃራኒ እንዳልሆነ ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው። እንግሊዝ አገር ውስጥ ወይም በሌሎች አገሮች የሚኖሩ ቤተሰብ ካልዎት ለመጪው የእነሱን ወይም የእርስዎን ማመልከቻ ጋር ሊያያዝ ስለሚችል ስለነዚህ ሰዎች መረጃ መስጠት ይገባል።

የህግ አማካሪዎ የጥገኝነት ቃለ መጠይቅ በሚያደርጉ ግዜ የመገኘት እድሉ ዝቅተኛ ነው (ስለ ህግ አማካሪ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፡ ገጽ 5 ላይ ይመልከቱ)። ቃለ መጠይቅ በሚያደርጉበት ጊዜ የህግ አማካሪዎ ካልተገኘ፡ ቃለመጠይቁን በቴፕ እንዲቀዳ ባለሥልጣኖቹን ለመጠየቅ ይቻላሉ። ቃለ መጠይቁ በቴፕ ሬከርደር እንዲቀዳ የሚፈልጉ ከሆነ ቃለ መጠይቁ ከመጀመሩ 24 ሰዓቶች በፊት ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ከቃለመጠይቁ በኋላ ማንኛውም ያላቀረቡት አስፈላጊ መረጃ ካለ፡ ለህግ አማካሪዎ በተቻለ መጠን በፍጥነት መንገር ይገባል። የህግ አማካሪዎ ተጨማሪ የሆነ መረጃ ለማቅረብ አምስት ቀን ብቻ ነው የሚፈቀድለት።

## ቁጥጥር ሥር መዋልና ሪፖርት ማድረግ

ባለስልጣናቱ ለአንዳንድ ጥገኛ ጠያቂዎች በማንኛውም የጥገኝነት ጥያቄ ላይ እያሉ በቁጥጥር ስር እንዲቆዩ የማድረግ ሥልጣን አላቸው፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ቁጥጥር ስር ማስገባቱ ተገቢ እርምጃ እንደሆነማሳየት መቻል አለባቸው። አብዛኛው ጊዜ ባለሥልጣናቱ ሰዎቹን በቁጥጥር ስር እንዲቆዩ የሚያደርጉበት ምክንያት የጥገኝነት ጥያቄያቸውን በተመለከተ ቶሎ ብለው ውሳኔ ለመስጠት ከፈለጉ ወይም ደግሞ ያመለከተው ሰው ተመልሶ አይመጣም ብለው ከጠረጠሩ ነው።ባለሥልጣኖቹ በቁጥጥር ስር እንዲቆዩ ከወሰኑ፡ ለምን ቁጥጥር ስር እንዲቆዩ እንደተፈለገ በጽሑፍ ሊነግሮት ይገባል። ውሳኔአቸውን ደግሞ መቃወም ይችላሉ። ነጻ እንዲለቁዎት ለመወያየት ደግሞ፡ ህጋዊ የሆነ ምክር ማግኘት መቻል አለብዎት። የኢሚግሬሽን እስረኞች ዋስትና (Bail for Immigration Detainees – (BID) የሚባለው ማህበር ወይም ደግሞ በእስር ቤት ያሉ ሰዎችን የሚጠይቁ ጠያቂ ቡድን ከእስር ቤት እንዲለቀቁ እንዴት መወያየት እንደ ምትችሉ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ። እባክዎን የ BID ድርጣቢያ (ድረገጽ) በ http://www.biduk.org ይመለከቱ ወይም በስልክ ቁጥር 020 7247 3590 መደወል ይችላሉ።

አብዛኞቹ ቁጥጥር እንዲቆዩ ያልተደረጉ የጥነኝነት ፈላጊዎች ወደ ሪፖርት ማእከል በመሄድ በመደበኛው ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። ሪፖርት ለማድረግ ከሶስት ማይል በላይ የሚራመዱ ከሆነ የጉዞ ወጪ እንዲከፈልዎት ለመጠየቅ የቻላሉ።

### ውሳኔ ለማግኘት በምጠብቅበት ጊዜ ምን ይከሰታል?

UKBA በሚጠይቁት መሰረት እያንዳንዱ ቃለመጠይቆች ላይ መሳተፍ ይገባል። የሚሰጥዎትን ቅጽ በሙሉ በጊዜየው ሞልተው መመለስ ይገባል። ይህን ተግባር ሳይፈጽሙ ከቀሩ ግን፡ UKBA የሚጠይቁትን ነገር አላሟሉም ብለው ስለሚያስቡ፡ የጥገኝነት ጥያቄዎን ላይቀበሉት ይችላሉ። በዚህ ጊዜ አድራሻዎን ከቀየሩ፡ UKBA ማሳወቅ በጣም አስፈልጊ ነው። ይህም ራስዎ ሊያደርጉት ይችላሉ ወይም የህግ አማካሪዎ እርስዎን በመወከል እንድያደርግሎት መጠየቅ ይችላል።

### ያቀረብኩት ጉዳይ ተቀባይነት ካላገኘ ምን ይከተላል?

አብዛኛውን ጊዜ አብዛኞቹ እነዚህ የሚቀርቡት የጥገኝነት ማመልከቻዎች ተቀባይነት እንኳን ባይኖራቸው አንዳንዱ ግን በይግባኝ በኋላ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ያቀረቡትን የጥገኝነት ጥያቄ UKBA ካልተቀበሉት፡ አንዳንዶቹ የጥገኝነት ጠያቂዎች ከእንግሊዝ አገር ከወጡ በኋላ ብቻ ይግባኝ ማለት የሚፈቀድላቸው ቢሆንም እንኳን፡ ፡ ይህን የተሰጥዎትን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለመጠየቅ ይችላሉ። እንዲቆዩ የሚያስችልዎት ሌላ ምክንያቶች ካልዎት፡ ለምሳሌ ከእንግሊዝ አገር ለቀው እንዲወጡ ከተደረገ የሰብአዊ መብትዎ የሚጣስ ከሆነ ፤ በዚህ የይግባኝ ማመልከቻዎ ላይ መግለጽ አለብዎት። ይህ የግባኝ ጥያቄ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ብቻ ማስገባት ስላለብዎት፡ ከማድረግዎ በፊት ተሎ ብለው የህግ አማካሪዎን ማነጋገር ይገባል። ያቀረቡት ይግባኝ ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ፡ የ UKBA ጽህፈት ቤት አገሩን ለቀው እንዲወጡ ይጠበቅቦታል፣ በፍቃደኝነት አገሩን ለቀው ካልወጡ ደግሞ ባለሥልጣኖቹ በግድ ሊያስወጥዎት ይችላሉ

### ተጨማሪ ማረጋገጫዎችን ማቅረብ

ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ካላገኘና ተጨማሪ ይግባኝ የማለት መብት የሌልዎት ከሆነ እንግሊዝ አገር ውስጥ ለመቆየት የሚያስችልዎት ሌላ አዲስ ወይም ተጨማሪ ምክንያቶች ለማቅረብ ይችላሉ። ይህ ደግሞ 'ተጨማሪ ማረጋገጫ ማቅረብ' ተብሎ ይጠራል። ይህንን አሰራር በተመለከተ ግን የህግ ምክር ማግኘት አስፈላጊ ነው። ማንኛውም የሚቀርቡ ተጨማሪ ማረጋገጫዎች በአካል ብቻ መቅረብ አለባቸው።

**ያቀረቡትን የመጀመርያ የጥገኝነት ጥያቄ ከ5 መጋቢት2007 በፊት ያስገቡት ከሆነና** ተጨማሪ ማረጋገጫዎች ለማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ ወደ ሊቨርፑል ተጨማሪ ማረጋገጫ ማቅረብያ ክፍል Liverpool Further Submissions Unit ( FSU) በመሄድ በአካል ማቅረብ ይገባል። ይህን ለማድረግ አስቀድመው ወደ 0151 213 2411 በመደወል ቀጠሮ መያዝ ይገባል። ቀጠሮ ሳይዙ ወደ FSU የመጡ ከሆነ ግን እንዲመለሱ ይደረጋል። አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ መንገር አለብዎት።

**ያቀረቡትን የጥገኝነት ጥያቄ በ5 መጋቢት2007 ወይም ከዚህ ቀን በኋላ ያስገቡት ከሆነ፣** ተጨማሪ ማረጋገጫዎች ለማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ በሚኖሩበት ክፍለ ሃገር ላይ በሚደረገው የመደበኛ የማረጋገጫ ማቅረብያ ጊዜ ላይ ማቅረብ ይገባል።

ልዩ የሆነ ሁኔታ የሚያሟሉ አንዳንድ የጥገኝነት ጠያቂዎችች ይህ የሚያቀርቡት ተጨማሪ ማረጋገጫ በአካል መጥተው ሳይሆን በፖስታ እንዲልኩት ሊደረግ ይችላል። ስለሆነ እርስዎ በዚህ ረድፍ የሚገኙ መሆንዎን ለማረጋገጥ በአቅራብያዎ የሚገኘውን የሬፍውጅ ካውንስል ጽህፈት ቤትን መጠየቅ ይችላሉ።

### የጥገኝነት ጥያቄ አሰራር ሂደት

የእርስዎ ጉዳይ የተለየ ቢሆንም ቀጥሎ ያለውን ሰንጠረዥ ጠቅላላ የሆነ የጥገኝነት ሂደት ያሳያል – እባክዎን ስለ ጉዳይዎ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ምክር ሰጪ ሰራተኛውን ወይም የህግ አማካሪዎን ይጠይቁ።






**የህግ ምክር**

የሚያስፈግዎትን የህግ ምክር ከህግ ወኪሎች ሊያገኙ ይችላሉ። እነዚህ የህግ ወኪሎች ሶሊሲተር፡ ጠበቃ ወይም የህግ አማካሪዎች በመባል ይታወቃሉ። በቂ የሆነ ገንዘብ ከሌልዎት፡ ለነዚህ የህግ አማካሪዎች ላይከፍሉ ይችላሉ። የህግ አማካሪዎ ክፍያውንና ወጪውን መንግስት እንዲከፍለው ሊጠይቅ ይቻላል። ይህ አሰራር ደግሞ የህግ እርዳታ (legal aid) በመባል ይታወቃል። አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ደግሞ እነዚህ የህግ ወኪሎች ሊያዘጋጅሎት ይችላሉ።

ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ካጣና፡ የይግባኝ ማመልከቻ ለማስገባት ፈልገው ወደ እነዚህ የህግ ወኪሎች ከሄዱ፡ ወኪሎቹ ጉዳይዎ በቂ የሆነ ማስረጃ የለውም ብለው ካሰቡ፡ እርዳታ ላይሰጥዎት ይችላሉ። ይህ ካጋጠምዎትና ጠንካራ የሆነ ማስረጃ አለኝ የሚሉ ከሆነ ግን፡ ወደ ህግ አገልግሎት ኮሚሽን ጽህፈት ቤት (Legal Services Commission) በመሄድ ይግባኝ በማለት የህግ ወኪሉን ውሳኔ ሊቃወሙ ይችላሉ። ይግባኝ ለማስገባትም ይችላሉ። የህግ ወኪልዎ ደግሞ የይግባኝ ማመልከቻ ቅጽ በመስጠት የት ማስገባት እንዳለብዎት መረጃ መስጠት ይገባዋል። በስኮትላድ የሚኖሩ ከሆነ፡ የተለያዩ የህግ አሰራር አሉ። ስለዚህ ጉዳይ ረፍዩጂ ካውንስል በስኮትላንድ (Scottish Refugee Council) መጠየቅ ይችላሉ።

በእንግሊዝ አገር አንዳንድ ቦታዎች ላይ በጥገኝነት ፈላጊዎች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ የሕግ ወኪሎች ቁጥር የተወሰነ ነው። ይህ ማለት ደግሞ፡ የሕግ ወኪል ለማግኘት ወደ ሌላ ቦታ ሊጓዙ ይችላሉ ማለት ነው። የጥገኝነት ድጋፍ የሚቀበሉ ከሆነና በሚኖሩበት አከባቢ የህግ ወኪል ከሌለ፡ ወደ ህግ አማካሪዎ ለመሄድ የሚያወጡትን ወጪ የህግ አማካሪዎ ሊከፈል ይችላል፡፡

የጥገኝነት ጥያቄ ካቀረቡ ወዲህ ወደ ሌላ አከባቢ የመኖርያ ቤት የሚቀይሩ ከሆኑ፡ አብዛኛው ጊዜ በአከባቢው ሊገኝ የሚችል የህግ ወኪል ማግኘት ይገባል። ምክንያቱ ወደ ህግ አማካሪዎ ለመጓጓዝ ቀላል ላይሆን ስለሚችል።

ጥሩ የሆነ የህግ ምክር ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የሚመርጡትን የህግ ወኪል በኢምግሬሽን ህግ ላይ ከህግ አገልግሎት ኮሚሽን (Legal Services Commission – (LSC)) ግኑኝነት ያለው ማህበር አባል ቢሆን ወይም በኢምግሌሽን አገልግሎት ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት (Office of the Immigration Services Commissioner – (OISC)) ላይ የተመዘገበ አማካሪ ቢሆን ይመረጣል።

እነዚህ ማህበሮች ደግሞ ቀጥሎ ካሉት አርማዎች አንዱ ወይም ሁሉቱም ሊኖራቸው ይገባል።

በተጨማሪም ወደ OISC ጽህፈት ቤት በመሄድ ስለ ጥገኝነት ህግ ምክር ለመስጠት የተፈቀደላቸው ማህበሮች ስም ዝርዝር ለመጠየቅ ይችላሉ። ስልክ ቁጥር፡ 0845 000 0046 ወይም http://www.oisc.gov.uk ላይ ለማንበብ ይችላሉ።

**የእንግሊዝ አገርና የዌልስ የህግ ምክር**
የአከባቢ የህግ ምክር (Community Legal Advice) በእንግሊዝ አገርና በዌልስ የሚገኙትን የህግ ወኪሎች ዝርዝር ያወጣል። ስልክ ቁጥር: 0845 345 4345 ወይም http://www.communitylegaladvice.org.uk ላይ ለማንበብ ይችላሉ።

**የስኮትላድ የህግ ምክር**

የስኮትላድ የህግ ማህበር (Law Society of Scotland) በስኮትላንድ የሚገኙትን የህግ ወኪሎች ዝርዝር ያወጣል። ስልክ ቁጥር፡ 0131 226 7411 ወይም http://www.lawscot.org.uk ላይ ለማንበብ ይችላሉ።

**የሰሜናዊ አይርላንድ የህግ ምክር**

የሰሜናዊ አየርላድ የህግ አገልግሎት ኮሚሽን (Northern Ireland Legal Services Commission) በሰሜን አየርላንድ የሚገኙትን የህግ ወኪሎች ዝርዝር ያወጣል። http://www.nilsc.org.uk ላይ ለማንበብ ይችላሉ።

## የህግ ወኪል ለማግኘት የሚያስችሉ ሌሎች መንገዶች

**የጥገኝነት እርዳታ (Asylum Aid)** – http://www.asylumaid.org.uk

የምክር መስመር: 020 7354 9264ሰኞ: 2 – 4.30 ከሰዓት በኃላ ሓሙስ: 10 ጥዋት– 12.30 ከሰዓት በኃላ

**የኢምግሬሽን ህግ ሰራተኞች ማህበር (Immigration Law Practitioners Association)** – www.ilpa.org.uk

**የህግ ማእከላት ፌደሬሽን (Law Centres Federation)** – http://www.lawcentres.org.uk

**ባልዎት የህግ ወኪል ደስተኛ አይደሉም ወይ?**

ባልዎት የህግ ወኪል ደስተኛ ካልሆኑና ጉዳይዎን በደምብ አላቀረቡትም ብለው ካሙኑ ወደ የኢምግሬሽን አገልግሎት ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት በመሄድ መክሰስ ይችላሉ። ስልክ ቁጥር፡ 0845 000 0046 ወይም ቀጥሎ ባለው ድርገጻቸው ሂደው ለማንበብ ይችላሉ፡ www.oisc.gov.uk

***በዚህ ጽሁፍ ያሉትን መረጃዎች ለመመርያ እንጂ ስላለው ህግ ሙሉ መግለጫ አይሰጡም። እባክዎን ዝርዝር የሆነ ምክር የሚፈልጉ ከሆነ ከህግ አማካሪ ጋር ይነጋገሩ።***

Asylum Support Partnership consists of:

North of England Refugee Service, charity number: 1091200 www.refugee.org.uk
Refugee Action, charity number: 283660 www.refugee-action.org.uk
Refugee Council, charity number: 1014576 www.refugeecouncil.org.uk
Scottish Refugee Council, charity number: SC008639 www.scottishrefugeecouncil.org.uk
Welsh Refugee Council, charity number: 1102449 www.welshrefugeecouncil.org